የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፱ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No 39.
ADDIS ABABA 27th May, 2008

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፫/፪ሺህ ዓ.ም

በኢትዮጵያ/ናይል ተፋሰስ ኢንሽዬቲá- የኤሌክትሪክ ኃይል ኤክስፖርት ፕሮጀክት፡ ኢትዮ-ሱዳን ኢንተርኮኔክሽን ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፬ሺ፩፻፲

CONTENTS

Proclamation No. 583/2008

International Development Association Financing Agreement for Ethiopia/Nile Basin Initiative Power Export Project, Ethio-Sudan Interconnector Ratification Proclamation Page 4110

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፫/፪ሺህ

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ/ናይል ተፋሰስ ኢንሽዬቲá-ለኤሌ ክትሪክ ኃይል ኤክስፖርት ፕሮጀክት ኢትዮ-ሱዳን ኢንተርኮኔክሽን ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፳፮ሚሊዮን፬፻፵ሺ ኤስ.ዲ. አር /ሃያ ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ አርባ ሺህ ኤስ.ዲ. አር./ የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘውን የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፲፯ ቀን ፪ሺህ፰ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራ ላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ ፴ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 583/2008.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** a Financing Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit in an amount SDR 26,440,000 (twenty six million four hundred forty thousand Special Drawing Rights) for financing Ethiopia/Nile Basin Initiative Power Export Project, Ethio-Sudan Interconnector was signed in Addis Ababa on the 17th day of January 2008;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its session held on the 8th day of May, 2008;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ/ናይል ተፋሰስ ኢንሽዬቲá- የኤሌክትሪክ ኃይል ኤክስፖርት ፕሮጀክት ኢትዮ-ሱዳን ኢንተርኮኔክሽን ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኀበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፫/፪ሺህ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኀበር መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፲፯ ቀን ፪ሺህ፰ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 4375ET የብድር ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፳፮ሚሊዮን፬፻፵ሺ ኤስ.ዲ.አር /ሃያ ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ አርባ ሺህ ኤስ.ዲ.አር./ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፱ ቀን ፪ሺ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for Ethiopia/Nile Basin Initiative Power Export Project, Ethiopia-Sudan Interconnector Ratification Proclamation No. 583/2008".

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement Credit Number 4375-ET signed in Addis Ababa on the 17th day of January 2008 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of SDR 26,440,000 (twenty six million four hundred forty thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 27th day of May, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**